## <u>ዱዋል ላንጉዌጅ/ቱ ዌይ ኢመርሽን</u>

የፕሮግራም መግለጫ:- ዱዋል ላንጉዌጅ/ቱ ዌይ ኢመርሽን፣ እንግሊዝኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያልሆኑ ተማሪዎች የእንግሊዝኛም ሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን አቀላጥፈው እንዲናገሩ ብሎም ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ የሚረዳ ፕሮግራም ነው። እንግሊዝኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያልሆነ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ተማሪዎችና እንግሊዝኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆነ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ተማሪዎች አንድ ላይ ሆነው በሁለቱም ቋንቋዎች ይማራሉ። የሁለቱም ቡድኖች ተማሪዎች በሁለቱም ቋንቋዎች የማንበብና የመጻፍ ክህሎትን ያዳብራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ፕሮግራሙ፣ ተማሪዎች በቀለም ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዳል። ትምህርቱ ለመመረቅ የሚያስፈልገውን ብቃት እንዲያሟሉም ይረዳቸዋል።

<u>የትምህርቱ ዓላማዎች:-</u> ከክፍል ወደ ክፍል ለመዛወር የሚያስፈልገውን የቀለም ትምህርት መስፈርት ማሟላት እንዲሁም የሁለት ቋንቋ ክህሎትን ማዳበርና በሁለት ቋንቋ ማንበብና መጻፍን ማስተማር።

<u>የፕሮግራሙ ክፍሎች:-</u> ልጅዎ ከዚህ በታች ምልክት በተደረገባቸው መስኮች ትምህርት ያገኛል/ታገኛለች:-

_____ እንግሊዝኛ ማንበብና መጻፍ

_____ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ

_____ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልዩ ስልጠና (ESL)

_____ ሒሳብ በእንግሊዝኛ

_____ ሒሳብ በአፍ መፍቻ ቋንቋ

_____ ሳይንስ በእንግሊዝኛ

_____ የኅብረተሰብ ጥናት በእንግሊዝኛ

_____ የኅብረተሰብ ጥናት በአፍ መፍቻ ቋንቋ

_____ የአገራቸውንና የዩናይትድ ስቴትስን ታሪክና ባሕል

_____ የአሜሪካን ታሪክ በእንግሊዝኛ

_____ የአሜሪካን ታሪክ በአፍ መፍቻ ቋንቋ

_____ የኮንሲውመር ትምህርት በእንግሊዝኛ

_____ የኮንሲውመር ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ

_____ የጤና ትምህርት በእንግሊዝኛ

_____ የጤና ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ

_____ የአሽከርካሪነት ትምህርት በእንግሊዝኛ

_____ የአሽከርካሪነት ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ

<u>መውጣትን የሚመለከት አሠራር</u> **(በዚህ ክፍል ሥር ያለው መረጃ ከዲስትሪክት ወደ ዲስትሪክት ይለያያል::)**

ትምህርት ቤቱ የዱዋል ላንጉዌጅ/ቱ ዌይ ኢመርሽን ፕሮግራም የሚያካሂደው በክፍል _____ ለሚገኙ ተማሪዎች ነው። ፕሮግራሙ በእንግሊዝኛም ሆነ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ክህሎትን የሚያዳብር ስለሆነ ተማሪዎቹ እንግሊዝኛን አቀላጥፈው መናገር ቢችሉም እንኳን በፕሮግራሙ ውስጥ እንዲቀጥሉ ይደረጋል። የዲስትሪክታችን የመደበኛ ትምህርት ዝውውር መጠን በዓመት _____ % ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

በዚህ ፕሮግራም ታቅፈው ከሁለተኛ ደረጃ ይመረቃሉ ተብለው የሚጠበቁት ተማሪዎች መጠን _____ ነው።

<u>ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች</u>

ለየት ያለ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱ የተማሪውን የግል ትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP)) አላማዎች የሚያሳካ ይሆናል።

<u>በትምህርት ቤቱ የሚካሄዱ ሌሎች ፕሮግራሞች</u>

- እንግሊዝኛ አቀላጥፈው ለሚናገሩ ተማሪዎች መደበኛ ትምህርት ይሰጣል። በማንኛውም ጊዜ ትምህርቱ የሚሰጠው በእንግሊዝኛ ይሆናል። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጥቅም ላይ አይውልም። እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመቁጠር የሚሰጥ ትምህርት አይኖርም። የትምህርቱ አላማ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዘዋወርና ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን አግባብ ያለው የቀለም ትምህርት መስፈርት ማሟላት ነው።
- የሚካሄዱ ሌሎች ፕሮግራሞችን በተመለከተ መረጃ ካለ አባሪ ሆኖ ይያያዛል።